



# መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ

ትምህርት 5 ለ ሚያዝያ 24፣ 2018




“ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል
የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ
አይመለስም።” (ኢሳይያስ 55፡11)
HOLY BIBLE

“በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ” (2 ጴጥ 1:21) መልዕክታቸውንም በመጽሐፍ ቅዱስ ገፆች ላይ መዘገቡ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሕይወትን፣ ተስፋን፣ ብርታትንና መጽናናትን የሚሰጡ ወድ ዕንቆዎችን እናገኛለን ... አንዳንዶቹ ወዲያውኑ ተለይተው የሚታዩ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በማስተዋል ሊፈለጉ ይገባል።

እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለእኛ ያዘጋጃቸውን እነዚህን ዕንቁዎች ቆፍረን የምናወጣው እንዴት ነው? መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበብ የምናገኛቸው ጥቅሞች ምንድናቸው?







የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን:

- ጊዜ
- ሥፍራ
- የአጠናን ስልት

መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት ጥቅሞች:

- የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልን የማጋራት ጥቅሞች
- መጽሐፉን የመብላት ጥቅሞች


# የመጽሐፍ ቅዱስ

# አጠናን



# ጊዜ

“እናንተ ትሹኛላችሁ፥ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ።” (ኤርምያስ 29:13)






መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ሁነኛው ጊዜ መቼ ነው?

ምላሽ ስንሰጥ ሁለት ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት። እነርሱም የቆይታ ጉዳይና የጥራት ጉዳዮች ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት አምስት ደቂቃን ብቻ ከምንመድብ በቀን ውስጥ ለአንድ ሰዓት ለጥናት ብንለይ ይበልጥ ተጠቃሚዎች እንደምንሆን ግልጽ ነው።




ቢሆንም ግን ለማጥናት የምንመድበውን ጊዜ እንዲሁ ከላይ ከላይ ብቻ በማንበብ መጨረስ የለብንም። ለማንበብ የተነሳሳንበት ምክንያት ቁልፍ ሚና የሚጫወተው እዚህ ጋር ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የምናነብበው ለምንድን ነው? እንዲሁ እውቀትን ፍለጋ ነው ወይስ እግዚአብሔርን ለማወቅ ካለን ጥልቅ ምኞት የተነሳ ነው?

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ትልቁን ጥቅም የምናገኘው ጊዜው ከእግዚአብሔር ጋር ለማሳለፍ የምንወስደው ጊዜ ሲሆን (ኤር 29:13)፣ በእርሱ ስንደሰት (መዝ 37:4) እና በገፆቹ ውስጥ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የተለየ መልዕክት ስንፈልግ ነው።

# ሥ ፍ ራ

“ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ።” (ማርቆስ 1:35)

ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ጊዜን ለማሳለፍ ሲፈልግ በማለዳ ፀሐይ ሳትወጣ ተነስቶ ጸጥ ወዳለ ስፍራ ይሄድ ነበር (ማር 1:35)። ይህ ለጸሎት ደግሞም ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚጠቅም ነው።





ረብሻ ወይም ሩጫ በበዛበት ስፍራ በጥናታችን ላይ ማተኮሩ የሚከብድ ነገር ነው። ይህን ለማድረግ የሚመረጠው ምቹ፣ ጸጥ ያለና ገለልተኛ በሆነ ቦታ ነው።

የቀኑ የመጀመሪያ ወይም የመጨረሻ ሰዓታት ፀጥ ያሉ ስለሚሆኑ ሀሳባችንን በእግዚአብሔር ላይ ለማተኮር ተመራጭ ጊዜያት ናቸው።





ትክክለኛውን ጊዜና ሥፍራ ካገኘን በኋላ ይህን ተግባር ሳናቋርጥ በመደበኛነት እናድርገው። ምናልባት ይህን ጊዜ በተለየ ጉዳይ ምክንያት ልናቋርጠው ብንችልም ዕለታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችንን ሳናደርግ ግን ብዙ ቀናትን ማሳለፍ የለብንም።



# የአጠናን ስልት (1)

"ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።" (ኢሳይያስ 55:11)

## ጥልቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እነዚህን አራት ክፍሎች ይይዛል

### መጸለይ

- በጥናታችሁ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ መሪ እንዲሆን ጋብዙት
- እርሱ ልባችሁንና አሳባችሁን በመንካት የምታነብቡትን እንድታስተውሉ ያደርጋል

### ማንበብ እና መረዳት

- ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ጥቅስ ወይም ክፍል ምረጡ
- በአሳባችሁ ውስጥ እንዲቀረፅ በእጃችሁ ፃፉት
- ቁልፍ ነጥቦችን አስምሩባቸው
- ለእነዚህ ቁልፍ ነጥቦች መነሻ የሆኑ ሃሳቦችን ፃፏቸው

### መጸለይ

- እግዚአብሔር የተማራችኋቸውን ሃሳቦች እንድትተገብሯቸው እንዲያግዛችሁ ጸልዩ

### ማጋራት


- የተማራችሁትን ለማን ማጋራት እንደምትችሉ አስቡ





# የአጠናን ስልት (2)


"ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም።" (ኢሳይያስ 55:11)



## ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ስልቶች

- አንድን ጥቅስ ከሌላ ጥቅስ ጋራ ማነፃፀር (ኢሳ 28:10)
- አንድን ምዕራፍ ወይም አንድን መጽሐፍ አንብቦ መጨረስ
- ስለ አንድ ርዕስ ወይም ቃል ኮንኮርዳንስ በመጠቀም ማጥናት
- የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሜንቴሪዎችንና መዝገበ ቃላትን መጠቀም
- በተጓዳኝ ደግሞ "የዘመናት ተጋድሎ" ከሚለው የኤለን ጂ ኋይት የመፃሕፍት ስብስብ ሃሳቦችን መውሰድ





# መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት ጥቅሞች



# የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልን የማጋራት ጥቅሞች

"የደከመውን በቃል እንዴት እንደምደግፍ አውቅ ዘንድ ጌታ እግዚአብሔር የተማሩትን ምላስ ሰጥቶኛል፤ ማለዳ ማለዳ ያነቃኛል፥ እንደ ተማሪዎችም ትሰማ ዘንድ ጆሮዬን ያነቃቃል።" (ኢሳይያስ 50:4)



እንበልና ለቅዳሜ የሰንበት አገልግሎት ስብከት እንድንዘጋጅ ተጠየቅን። በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ መርቶን የመረጥነውን ርዕስ በጸሎት ሆነን የምናጠናበትን ጊዜ እናመቻቻለን። ከዚያም ቅዳሜ ቀን በኃይል ሰበክን። ከዚህ ስብከት ትልቁን ጥቅም የሚያገኘው ማንነው?



በስብከት አገልግሎትም ሆነ በግል ከሌሎች ጋር የምንጋራው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጠቀሜታው በሁለት ጎን ነው።



በመጀመሪያ እኛ ከተማርነው ነገር እንጠቀማለን። ሁለተኛ ደግሞ የተማርነውን እውቀት የምናጋራቸው ሰዎች ይጠቀማሉ። በቃሉም ላይ በጥልቀት ለመመርመር ይደፋፈራሉ።





በሁለቱም ሁኔታዎች ላይ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት እየጠነከረና እየጠለቀ ይሄዳል። "በከንቱ አይመለስም" የተባለለት የእግዚአብሔር ቃል ይህን ያህል ኃያል ነው (ኢሳ 55:11)።

# መጽሐፉን የመብላት ጥቅሞች

"ቃልህ ለጕሮሮዬ ጣፋጭ ነው፤ ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ።" (መዝሙር 119፥103)




የእግዚአብሔርን ቃል መብላት ያስፈልገናል (ኤር 15:16)!

ቃሉ ከማር ወለላ ይልቅ ጣፋጭ ቢሆንም ገፆቹን እንበላለን ማለት ግን አይደለም (መዝ 119:103)። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ለነፍሳችን ምግብ ነው። መንፈሳችንን የሚፈውስ እውነተኛ አዳሽና ባህሪያችንን የሚለውጥ ነው።

ደግሞ የሚገርመው ይህ ምግብ ነፃ መሆኑ ነው (ኢሳ 55:1)!

ማድረግ የሚጠበቅብን ወደ እግዚአብሔር ቀርበን እርሱ በቃሉ የሚለንን ማዳመጥ ብቻ ነው (ኢሳ 55:3)። በቃሉ ውስጥ ጠልቀን ይበልጥ ጊዜን ባሳልፍን ቁጥር በይበልጥ እንገነባለን እናም ብዙ በረከትን እናገኛለን።



"የሰው የአዕምሮ ልህቀት ምንም ያህል ቢሆን የሚበልጥ ብርሃንን ለማግኘት መፃሕፍትን በጥልቀትና በቀጣይነት መመርመር አያስፈልግም ብሎ ማንም እንዳያስብ። እንደ ሕዝብ ሁላችንም በየግላችን የትንቢት ተማሪዎች እንድንሆን ተጠርተናል።"
Ellen G. White, Counsels to Writers and Editors, ገጽ 41

“ቃሉ እንዲሁ ቢነበብ ሰማይ ያቀደውን ውጤት አያስገኝም፤ ቃሉ መጠናትና በልብ ውስጥ መወደድ አለበት። እግዚአብሔርን ማወቅ በአዕምሮ ጥረት ሳይደረግ የሚደረስበት አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንድንረዳ ያግዘን ዘንድ እግዚአብሔርን እየጠየቅን መጽሐፍ ቅዱስን በትጋት ማጥናት አለብን። አንድ ጥቅስን ወስደን እግዚአብሔር በጥቅሱ ውስጥ ለእኛ ያስቀመጠልንን ፍሬ ነገር በማውጣት ላይ አሳባችንን ማተኮር አለብን። [...] የእግዚአብሔር ቃል የሕይወት እንጀራ ነው። ይህን ቃል የሚበሉና የሚዋሃዳቸው ሰዎች የእያንዳንዱ ድርጊታቸው አካልና የእያንዳንዱ ባህሪያቸው መገለጫ ባደረጉት ጊዜ በእግዚአብሔር ብርታት ይጠነክራሉ። ቃሉ ለነፍስ የማይሞት ንቃትን ይሰጣል፣ አረማመድንም ያጸናል እናም ለዘላለም የሚቆይ ደስታን ይሰጣል።

EGW (Lift Him Up, April 7)